የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት አገልግሎት

# ቆየት ያሉ የጋዜጦች ሕትመት

## ከክምችት ክፍሉ

## 6ኛ እትም



# መግቢያ

የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት አገልግሎት አብይ ተልዕኮ በሀገራችን ያለውን የሰነድ ሥራ አመራር በማዘመን እና ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት ማናቸውም አይነት የመረጃ ሀብቶች(መዛግብት፣ጥንታውያን የጽሑፍ ቅርሶች፣ መጻሕፍትና ሌሎች የታተሙና ያልታተሙ ሰነዶች) ተሰባስበው፣ ተደራጅተው እና ተጠብቀው ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ፣ ለጥናትና ምርምርሥራ ጥቅም ላይ እንዲውሉ እንዲሁም ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ ነው።ከዚህ በተጨማሪም ኤጀንሲው የቤተመጻሕፍትና የሰነድ ሥራ አመራር ሙያዎች እንዲስፋፉ የበኩሉን አስተዋጽዖ በመወጣት ላይ ይገኛል። ለዚህም በቤተመጻሕፍት እና በሰነድ ሥራ አመራር ሙያዎች አጫጭር የሥራ ላይ ስልጠናዎችንና የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐግብሮችን በማዘጋጀት እንደሀገር በመረጃ፣ በዕውቀትና በክህሎት የጐለበተ ህብረተሰብ ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ ነው።

ተቋሙ ከሰባ ዓመታት በላይ ለበርካታ አንባቢዎች፣ ለተመራማሪዎች፣ ለደራሲዎች፣ ለጋዜጠኞች እና ለሌሎች ደንበኞች ዘርፈ ብዙ የመረጃ ሀብቶችን በማቅረብ እና አገልግሎት በመስጠት በሀገራችን ዋነኛ የዕውቀት ምንጭ ሆኖ ቆይቷል። ከዚህ አንጻር አሁን ላይ የተለያዩ ሀገራዊ ሰነዶችን/መዛግበቶችን፣ ጥንታዊ የጽሑፍ ቅርሶች /MANUSCRIPTS/፣ ፎቶግራፎችን፣ ካርታዎችን፣ የድንበር ስምምነቶች፣ የህትመት ውጤቶችን (መጻሕፍት፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ የድምጽ፣ የድምጽና ምስልና የመሳሰሉትን)፣ ፖስተሮችን፣ የሠርግ ጥሪ ወረቀቶችን፣ የ40 ቀን መታሰቢያ ካርዶችንና የመሳሰሉትን በማከማቸትና ጠብቆ በማቆየት ለአገልግሎት እያዋለ ይገኛል። ኤጀንሲው በስሩ የሚገኙ የመረጃ ሀብቶችን ለአገልግሎት ከማቅረብ ባሻገር በተለያዩና በተሰጡት ተልዕኮዎች ዙሪያ የሚያተኩሩ ሕዝበ ገለፃዎችን /LECTURES/፣ ጉባዔዎችን /SEMINARS/፣ አውደ-ርዕዮች/EXHIBITIONS/ እና የንባብ ሳምንታት/READING WEEKS/ በማዘጋጀት ያሰባሰባቸውን የመረጃ ሀብቶች ለዜጐች የማስተዋወቅ እና በሀገራችን የንባብ ባህል እንዲያድግ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ይህ የቆዩ ጋዜጦች ፎቶ ህትመትም ከኤጀንሲው በርካታ ስብስቦች መካከል የሆኑትንና ለዘመናት ተከማችተው የሚገኙትን ጋዜጦች ለማስተዋወቅ የተዘጋጀ ሲሆን ኤጀንሲው ስብስቦቹን ለማስተዋወቅ የሚያደርጋቸው ጥረቶች አንዱ አካል ነው።

ጋዜጦችን የመሰብሰብ፣ የማደራጀትና ጠብቆ ለትውልድ የማስተላለፍ ልምድ በውጭው ዓለም እጅጉን የተለመደ ነው። በተለይ በእንግሊዝ ከ1665 ጀምሮ በተለያየ መልኩ መረጃን ሊገልጹ የሚችሉ ጋዜጦችን በመዛግብት ክምችት ክፍላቸው ውስጥ በማጠራቀም ማንነታቸውንና ታሪካቸውን ጠብቀው ለትውልድ ማስተላለፍ ችለዋል። ከዚህ አንጻር በሀገራችን የቆዩና ታሪካዊ ጋዜጦችን የማሰባሰብ ባህላችን በተለያዩ ፖለቲካዊ ግጭቶችና በጉዳዩ ላይ በቂ ግንዛቤ ያለመያዝና በሌሎችም ችግሮች ምክንያት ደካማ መሆኑ ይታወቃል። አሁንም ቢሆን በተለይ በክልሎች በተለያዩ ቋንቋዎች የሚታተሙ ጋዜጦች አሁንም በሚፈለገው ደረጃ እየተሰባሰቡና ተደራጅተው ለትውልድ በሚተላለፉበት መልኩ እየተቀመጡ አይደለም። የዚህ ሕትመት አዘጋጆች የክልል ባህል ቢሮዎችን እንዲሁም ጋዜጦችንና መጽሔቶችን የሚያሳትሙ አካላትን ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው እንዲንቀሳቀሱ ማስታወስ ይፈልጋሉ። ጋዜጦችን አሰባስቦና ጠብቆ ማቆየት በርካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።"ወደ ፊት ለመስፈንጠር ወደ ኋላ መንደርደር" እንደሚባለው እነዚህ ጋዜጦች የኋላው ታሪካችን ምን እንደሚመስል በማሳየትና የቀድሞ አባቶቻችን የሠሩት ሥራ ምን እንደሆነና ጠቃሚነቱን እንድንረዳና ግንዛቤ እንድንወስድ ጉድለቱንም እንዲንናገር በማድረግ አሁን የምንገኘው ትውልዶች በዚህ ወቅት ለምናከናውናቸው ሥራዎች የሞራል ስንቅ በመሆን አውንታዊ ሚና ይኖራቸዋል። ጋዜጦቹ በሙዚየም ውስጥም ሆነ በሌሎች ቦታዎች በዐውደ-ርዕይነት ለማሳየት፣ ለተማሪዎች ለትምህርት ማስረጃ ማሳያነት፣ ለመገናኛ ብዙሀንና ለጋዜጠኞች (መረጃ ለሚፈልጉ) እንደ መጀመሪያ የመረጃ ምንጭነት ለመጠቀም፣ ለምሁራንና ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ የመረጃ ምንጭ በመሆን፣ ለአርቲስቶችና ፊልም ለሚሠሩ ድርጅቶች፣ በተለይ ለኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር ደግሞ የሙያ አጋሮቻቸውን ሥራ ለመዘከር፣ አሁን በሥራ ላይ ላሉ ጀማሪ ጋዜጦኞች የሙያ ልምድ መቅሰሚያ በመሆን ወዘተ እጅግ ጠቃሚ ናቸው።

የኤጀንሲዉ የጋዜጦች ስብስብ በንጉሠ-ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ስትታተም ከነበረችው አዕምሮ ጋዜጣ ጀምሮ እስካለንበት ዓመት (2014 ዓ.ም) የታተሙና የተሰራጩ በርካታ የጋዜጦች ስብስቦችን ይዞ ይገኛል። ክምችቱ ዘረፈ-ብዙ የሆነ ኢኪኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ ታሪካዊ ምርምሮችን ለሚያደርጉ አካላት ከፍተኛ የሆነ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ከማገልገሉ በተጨማሪ ታሪካቸውን ለማወቅም ሆነ ለተዝናኖት ንባብ ለሚመጡ ተገልጋዮች አገልግሎት ይሰጥበታል።

በዚህ ሕትመት ሀገራችን በታሪኳ ካሳለፈቻቸውና በኤጀንሲው የክምችት ክፍል ከሚገኙ ጋዜጦች መካከል የተወሰኑትን ፎቶግራፍ በማንሳት እንዲታተሙ ተደርጓል። የሕትመቱ ዋና ዓላማ ኤጀንሲው አሰባስቦና ጠብቆ ከያዛቸው የጋዜጣ ስብስቦች መካከል የተመረጡትን በማሳተም እና በማሰራጨት ስብስቦቹ እንዲተዋወቁ ማድረግ ነው። በተጨማሪም የተመረጡት ጋዜጦች አንባቢ ያለፈውን የሀገራችንን ታሪክና ትዝታ በምናብ እንዲያስብና እንዲያስታውስ ያደርጋሉ የሚል እምነት ስላለን በኤጀንሲው ከሚገኙ ክምችቶች መካከል ለዚህ ህትመት አስፈላጊ የሆኑትን በመምረጥ ለህትመት አብቅተናቸዋል። በዚህም መሠረት የዚህ የቆዩ ጋዜጦች ህትመት ይዘት በኢትዮጵያ ከመጀምሪያው የመንግስት ጋዜጣ -አዕምሮ- እስከ አሁን ድረስ በሕትመት የዘለቁትን የሚያካትት ሲሆን የመንግስታት ልሳኖች የነበሩ ጋዜጦችን፣ በግል ዘርፍ ይታተሙ የነበሩ ጋዜጦችን እንዲሁም በየጊዜው ሲታተሙ የነበሩ የስፖርት ጋዜጦች ተካተውበታል።

በዚህ ቅጽ የታተሙት የጋዜጦች ፎቶግራፎች ውስን በመሆናቸው ሁሉንም በክምችት ክፍላችን የሚገኙ የቆዩ ጋዜጦች ስብስብ ሙሉ በሙሉ የሚወክሉ አይደሉም። ሥራው በጋዜጦች ላይ የተሠራ የመጀመሪያ ሕትመት ሲሆን በቀጣይ ተመሳሳይ ቅጾችን በማውጣት ስብስቦቹን በስፋት የማስተዋወቅ ሥራ የሚቀጥል ይሆናል። ኤጀንሲው በዚህ አጋጣሚ በቆዩ ጋዜጦች ላይም ሆነ በሌሎች ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ አካላትም ሆነ ጋዜጠኝነት ለሚማሩ ተማሪዎች አብሮ ለመስራትና እናንተን ለማገልገል ያለውን ቁርጠኝትና ዝግጁነት ለመግለጽ ይወዳል።

በመጨረሻም ይህች አነስተኛ የቆዩ ጋዜጦች ፎቶግራፍ ሕትመት ለአንባቢያን ደርሳ ስሜትን በማጫር አንባቢያን ወደ ቤተመጻሕፍት በመምጣት ጋዜጦቹን እንዲያነብቡ ትገፋፋለች የሚል ትልቅ እምነት አለን።


መልካም ንባብ፤ መልካም ርዕይ!

የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት አገልግሎት

# ክፍል አንድ
# ታሪካዊ ዳራ

## 1.1 የጋዜጣ ምንነት

ጋዜጣ የሚለው ቃል "ጋዜታ" /GAZETTE/ ከሚለው ከጣሊያን ቃል የተወሰደ ሲሆን፣ ይህም ስያሜ የተሰጠው ለኢመደበኛ ዜና ወይንም ለመጀመሪያ ጊዜ በ16ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በቬኒሲያ ለሚታተመው የሃሜት ወረቀት ነው። ብዙም ሳይቆይ ተመሳሳይ ወረቀቶች በፈረንሳይ እና በእንግሊዝ መታየት ጀመሩ። ከግል የጋዜጣ አታሚዎች የመጣው የጋዜጣ ዓይነት በእንግሊዝ ከ16ኛው ክፍለ-ዘመን አጋማሽ በፊት የነበሩ ቢሆንም ሀተታቸው በዋናነት የዲፕሎማቲክ እንቅስቃሴዎች ዝርዝር ላይ ብቻ የተገደበ ነበር። ነገር ግን ንግስት ኤልዛቤት I ወደ ንግስና ስትመጣ፣ እንደዚህ ዓይነት የዜና ወረቀቶች በብዛት መታየት ጀመሩ። ይህም ሰፊው ህዝብ ጋር ለመድረስ ሲሆን፣ ሃሜትን፣ አሉባልታን፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚመጡ ይፋዊ ያልሆኑ ዜናዎችን፣ አዳዲስ የአሰሳ ዜናዎችን፣ የንግድ ማስታወቂያዎችን፣ እና የእለቱን አዝናኝ ዜናዎችን፣ አሰቃቂ የሆኑ የወንጀል ዜናዎችን፣ ተዓምራቶችን፣ ጥንቆላና አስማቶችን፣ እና የመሳሰሉትን ያካተቱ ነበሩ። በእነዚህ ወረቀቶች ላይ የሰፈሩት ዜናዎች የሚመጡት ከበጎ ፈቃደኞች ሲሆን ይህም በአብዛኛው ስማቸው ያልተጠቀሱ እማኞችን ዋቢ በማድረግ ሲሆን ኢተዓማኒ በመሆኑም ይታወቃል። ጋዜጣ የሚለው ቃል በ17ኛው ክፍለ-ዘመን የእንግሊዝ የመጀመሪያው እውነተኛ ጋዜጣ እንደሆነ ለሚታመነው እንደኦክስፎርድ ጋዜጣ (በ1665 የተመሠረተ) ለመሰሰሉት ለይፋዊ የመንግስት ህትመቶች በስፋት ጥቅም ላይ መዋል ጀመረ ::


Numb. 4.

The Oxford Gazette.

Published by Authority.

From Thursday November 23. to Monday November 27. 1665.

ምንጭ:- ox.ac.uk/gazette{1665 wood print

by granger fineart America .com


Numb. 198.

The London Gazette.

Published by Authority.

From Monday, August 24. to Thursday, August 27. 1668.

ምንጭ:- World First English News paper daily Email.Co.Uk


Ordinari Post Tijdender/
1645. den 9. Apr. N. 15.

Ifrån Hamborg den 19. Martij.


THE
New-England Courant.

MYSEVM BRITANNICVM

ምንጭ:- Post.ochnrinesTidningar_miniwand.com

## 1.2 የጋዜጣ ታሪካዊ ዳራ በኢትዮጵያ

### 1.2.1 ቅድመ 'አእምሮ'

አእምሮ ጋዜጣ ለንባብ የበቃበትን ጊዜ መሰረት አድርገን በኢትዮጵያ የጋዜጣ ሕትመት ታሪክ በትንሹ መቶ ዓመታት ሞልተውታል። አንድአንድ ጸሐፍት እንዲያውም በኢትዮጵያ ጋዜጣ የተጀመረበትን ጊዜ ወደ 19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ ይወስዱታል። እንደነሱ በሀገራችንጋዜጣ መታተም የጀመረው በ1880ዎቹ አጋማሽ ላይ ነበር። በ1890 ጣሊያኖች "ኤል ኤሪቴሬኦ" የሚል ስያሜ ያለው የሕትመት ሥራ ጀመሩ። እንዲሁም በ1891 "ኮሪኤሬ ኤሪቴሬኦ" የሚባል ጋዜጣ ለንባብ በቃ። በ1905 ዓ.ም በአማርኛ እና በፈረንሳይኛ የሚታተም "ሌ ሴሙኤር ዲኢቶፒ" የሚባል ጋዜጣ በሐረር መታተም ጀመረ። በ1912 "መልእክተ ሰላም" የሚባል ጋዜጣ በትግራይ ለህትመት በቃ። እነዚህ ጸሐፍት የሚጠቅሷቸው ጋዜጦች ግን በውጭ ዜጎች የተያዙና በአብዛኛው ሃይማኖታዊ ይዘት የነበራቸው ነበሩ።

### 1.2.2. አእምሮ-የመጀመሪያው የመንግስት ልሳን ጋዜጣ

በኢትዮጵያ ጋዜጣ ታሪክ ወሳኝ ጊዜ የነበረው የዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ሲሆን ለዚህ ምክንያቱ መደበኛ የመንግስት ጋዜጣ (ለምሳሌ'አእምሮ') መጀመሩና ጋዜጦችን በመጠቀም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ መነጋገር እና መጻፍ መጀመሩ ነው።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመንግስት ይፋዊ ጋዜጣ "አእምሮ"ይባላል።አእምሮ ጋዜጣ ህትመቱ የተጀመረው በ1906 ዓ.ም ነው። ነገር ግን ከዚህ ቀደም ብሎ ከ 1900ዓ.ም (እ.ኤ.አ) በፊት በአጼ ምኒልክ ቤተ-መንግስት በብላታ ገ/እግዚአብሄር በየእለቱ በእጅ እየተፃፈ የሚሰራጭ ወረቀት እንደነበር ይነገራል። የአእምሮ ጋዜጣ ህትመት የተጀመረው በንጉስ ምንሊክ ትእዛዝ ሲሆን የአርትኦት ስራውን የሚሰራው ነጋዴ የነበሩት አንድሬአስ ኤ ካቫዲአ የሚባሉ ግሪካዊ ነበሩ። በጊዜው ጋዜጣው ሲወጣ በሕዝቡ ዘንድ ጥልቅ አግራሞትን ፈጥሮ እንደነበር ይነገራል። ጋዜጣው የሚነበበው በንጉሱ ባለሟሎች፣ ከፍተኛ ሹማምንት እና መኳንንቶች በተገኙበት ነበር። አዕምሮ ጋዜጣ ሰምንታዊ ጋዜጣ የነበረ ሲሆን ለንባብ የሚበቃውም በየሳምንቱ ቅዳሜ ነበር። አዕምሮ እስከ ጣሊያን ዳግም ወረራ ዋዜማ ድረስ ሲነበብ ቆይቶ በ1927 ዓ.ም ተቋርጧል።

አዕምሮ ጋዜጣ ሲጀምር ሶስት ገጽ ዜና እና አንድ ገጽ ማስታወቂያን ያካተተ ነበር። ዜናው በአውሮፓ ስለ ጦርነት፣ ስለመሪዎች ጉብኝት እና በኢኮኖሚና ፓለቲካ ጉዳዮች ስለተደረጉ ስምምነቶች የሚያትት ነበር። በሀገር ውስጥ የንጉሱ የሥራ እንቅስቃሴ፣ ንግግሮች፣ አዋጆች በከተማው ውስጥ የተከሰቱ አዳዲስ ጉዳዮች እንዲሁም ለአሳታሚው የሚላኩ ደብዳቤዎች ይዳሰሱ ነበር። ጋዜጣው በ1924 እ.ኤ.አ አካባቢወደ ባለስምንት ገጽ ጋዜጣነት ከፍ ብሎ ነበር።ከ1924-1935 እኤአ በነበሩት እትሞቹ በዋነኛነት በወቅቱ የዓለም ሁኔታ ላይ ያተኮሩ ዘገባዎችን ያቀርብ ነበር።
የሀገር ውስጥ ዘገባዎቹን በሚመለከት የአእምሮ ጋዜጣ አብዛኞቹ ጽሁፎች የኢትዮጵያን አንድነት የሚሰብኩና የዘር ልዩነትን የሚያወግዙ ነበሩ። በተለይ የኢትዮጵያ አንድነት፣ የተሻለ ትምህርት ማግኘት ለስልጣኔ እና ለዘመናዊ የኑሮ ዘይቤ ያለውን ሚና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጭምር በማስደገፍ አጉልተው የሚያሳዩ ነበሩ። እንዲሁም ሀይማኖታዊ በዓላትን፣ የንጉሣዊ ቤተሰብ ጋብቻዎችን እና የልጆቻቸውን ልደት የሚዘግቡ ጽሑፎች ይታተሙበት ነበር። ከሐምሌ 20 1935 እኤአ ጀምሮ አእምሮ ጋዜጣ ጣልያን ኢትዮጵያን ለመውረር የነበራትን ምኞት የሚያጋልጡ ጽሁፎች ማተም ጀመሮ ነበር። አእምሮ በመጀመሪያ የስርጭት መጠኑ (በእጅ ተጽፎ!) 24 ኮቅጅዎች ብቻ የነበረሲሆን በ1929 እ.ኤ.አ. ወደ 200 ቅጂ ደርሶ እንደነበር ይነገራል።


AIMIRO
JOURNAL ETHIOPIEN
አእምሮ
SAMEDI
Directeur A. F. CAVADIA

የዳግማዊ ምኒልክን ምስል ያዘ የአእምሮ ጋዜጣ ቅጅ

## 1.2.3. ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ

ከአዕምሮ ጋዜጣ በኋላ በሁለተኛነት የሚመጣው ሀገር በቀል ጋዜጣ በ23/04/1917 ለንባብ የበቃው"ብርሃን እና ሰላም" ጋዜጣ ነው። ጋዜጣው ከ1927 እስከ 1932 ዓ.ም ሲነበብ የቆየ ሲሆን ዓመታዊ ክፍያውም 5 ብር ነበር። ብርሃንና ሰላም ታትሞ ለህዝብ የሚበቃው በየሳምንቱ ሐሙስ ነበር።

## 1.2.4 የቄሳር መንግስት መልክተኛ

የ1928ቱን የጣሊያን ወረራ ተከትሎ ሀገራችን በጣሊያን ቁጥጥር ስር ወደቀች። በጊዜውም ጣሊያኖች ለፕሮፓጋንዳ ሥራቸው የሚውል የራሳቸውን ጋዜጣ አቋቋሙ። ይህ የጣሊያኖቹ ጋዜጣ "ሮማ ብርሃን" ወይም "የቄሳር መንግስት መልክተኛ" ይባላል። ይህ ጋዜጣ ይወጣ የነበረበት ወቅት ሃገራችን ኢትዮጵያ በፋሽስቱ ጣሊያን በተወረረችበት ግዜ ሲሆን ጋዜጣው የወራሪው መንግስት በኢትዮጵያውያን ይነሳበት የነበረውን ተቃውሞና አመጽ ለማዳከም ሲጠቀምበት የነበረ ልሳኑ ነበር።

## 1.2.5. አዲስ ዘመን ጋዜጣ

ከነጻነት መመለስ በኋላ በሀገራችን በርካታ ጋዜጦች የተቋቋሙ ሲሆን ከእነዚህም መካከል "ሰንደቅ ዓላማችን" (1934-1941)፣"የኤርትራ ድምጽ" (1937-1944)፣ "የኢትዮጵያ ድምጽ" (1945- 1969)፣ "አዲስ ዘመን" እና "ኢትዮጵያን ሄራልድ" ይገኙበታል።

በ1933 ዓ.ም ንጉሠ-ነገሥት ኃይለሥላሴ "አዲስዘመን" የሚባለውንና በአማርኛ የሚታተመውን ጋዜጣ አቋቋሙ። ጋዜጣው "አዲስ ዘመን" የሚለውን ስያሜ ያገኘው ንጉሰ ነገስቱ ሚያዚያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም አዲስ አበባ ሲገቡ ከተናገሩት ንግግር ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይነገራል።በንጉሰ ነገስቱ ዘመን አዲስ ዘመን ጋዜጣ በቀን 10,000 ቅጂ ይታተም እንደነበር ታሪክ ያስረዳል። ጋዜጣው 60ኛ ዓመቱን ባከበረበት 1993 ዓ.ም እለታዊ ህትመቱ 40,000 ደርሶ ነበር።"አዲስዘመን" በየዘመኑ ዋነኛ የመንግስታት ልሳን ጋዜጣ በመሆን ሲያገለግል ቆይቷል።



የመጀመሪያው አዲስ ዘመን ጋዜጣ እትም በፊት ገጹ ይዞት የወጣው ፎቶ (ፎቶው ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ከስደት መልስ በአውቶሞቢል በክብር ወደ አዲስ አበባ ሲገቡ ያሳያል።)

## 1.2.6. ሠንደቅ ዓላማችን /"ባንዲራችን"/

የፋሽት ጣሊያን ወራሪን ከኢትዮጵያ ምድር ለማስወጣት በሱዳን ካርቱም የዘመቻ ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት "ባንዲራችን" የሚባል ጋዜጣተቋቁሞ ነበር። በብሪቲሹ መኮንን ፔሪይ ፎሎውስ (PERRY FOLLOWES) የተመሰረተውን ይህን ጋዜጣ በዋናነት ያዘጋጁት የነበሩት ታምራት አማኑኤል ሲሆኑ ዋና አዘጋጁ "ባንዲራችን" የሚለውን ስያሜ አይወዱትም ነበር። ምክንያታቸውም ስያሜው ከጣልያኑ "ባንዲራ" ከሚለው ቃል የመጣ መሆኑ ነበር። ከታምራት አማኑኤል በኋላ የባንዲራችን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆነው የሰሩት የብላቴን ጌታ ህሩይ ወ/ስላሴ ልጅ የነበሩት ሲራክ ህሩይ ናቸው።

በየሳምንቱ ረቡእ ለንባብ ይቀርብ የነበረው ባንዲራችን ጋዜጣ ዜናዎች ያተኮሩ የነበሩት የብሪትሽና የኢትዮጵያ የተባበረው ጦር በሚያስመዘግበው ድል እና በጣልያን ጦር ሽንፈት ላይ ነበር። ጋዜጣው ከታተመ በኋላ በአውሮፕላን በተለይም በጣልያን ይዞታ ስር በነበሩ የምእራብ ኢትዮጵያ ግዛቶች ይበተናል። በዚህም አማካኝነት ብዙ የጣልያን የቅኝግዛት ወታደሮች እንዲከዱ ማድረግ ይቻል እንደነበር ይነገራል። ንጉሠ-ነገሥት ኃይለ ሥላሴ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ "ባንዲራችን" የሚለው የቀድሞ ስም ተቀይሮ "ሰንደቅ ዓላማችን" በሚል ስያሜ እየታተመ



ሰንደቅ፡ዓላማችን

«ብሔራዊ በሆነየልማት እርምጃ ሕዝባችን ያደረገው ጥረትና ድካም ከመቸውም ይልቅ ጉልቶ ይታያል»

የሰንደቅ ዓላማችን ጋዜጣ አንድ ቅጅ

### 1.2.7. "ኢዮጵያን ሄራልድ" /Ethiopian Herald/

በትዮጵያ የመጀምሪያው በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚታተም ጋዜጣ የሆነው "ኢዮጵያን ሄራልድ" /Ethiopian Herald/ በ1943 ዓ.ም ለንባብ የበቃ ሲሆን አሁንም ድረስ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

### 1.2.8. በሪሳ ጋዜጣ /Gaazexaa Bariisa

የደርግ ዘመን ከቀደመው ስርዓት የወረሳቸው አዲስ ዘመን እና "ኢትዮጵያን ሄራልድ" የመሳሰሉ የመንግስት ልሳኖች እንድቀጥሉ አድርጓል። ከዚነዚህ በተጨማሪም ሌሎች ጋዜጦች ብቅ-ብቅ ብለው የነበረ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የመጀመሪያው የኦሮምኛ ጋዜጣ የነበረው በሪሳ ጋዜጣ ነው። በሪሳ ጋዜጣ ከ1969-1979 ዓ.ም በህትመት ላይ ቆይቷል። በተጨማሪም ሰርቶ አደር ጋዜጣ ከ(1972-1973) እና ሰረገላ ጋዜጣ (1973-1975) የመሳሰሉት ጋዜጦች ለንባብ የበቁ ሲሆን እነዚህ በአብዛኛው በደርግ ዘመን የሚወጡ ነበሩ። ከእነዚህ በተጨማሪ በዘመኑ በተለይ በአብዮቱ ማግስት በመንግስትም ሆነ የመንግስት ተቃዋሚ በነበሩ ድርጅቶች ባለቤትነት ይወጡ የነበሩት ጋዜጦችም የነበሩ ሲሆን "ዲሞክራሲያ"፤"ላብአደር"፤ "የሰፊው ሕዝብ ድምጽ"፤"ነሕ" የመሳሰሉት ተጣቃሽ ናቸው። እነዚህ ጋዜጦች በተለያዩ ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት የሚካሄድባቸው መድረክ መሆን ችለው የነበር ቢሆንም ይህ ነጻነት ግን የቆየው ለአጭር ግዜ ብቻ ነበር።

በሪሳ (Bariisaa) ትርጉሙ የአጥቢያ ኮከብ እንደማለት ነው።ይህን የመጀመሪያውን የኦሮምኛ ቋንቋ ጋዜጣ እነማን እንዳቋቋሙት በግልጽ ባይታወቅም Dhaabata Gaazexaa Bariisa (የበሪሳ ጋዜጣ ድርጅት) በሚል በግል የተቋቋመ ጋዜጣ ነበር። በመጀመሪያ ጋዜጣው ለጽሑፍ ይጠቀም የነበረው ቋንቋው ኦሮምኛ ሆኖ የአማርኛ ፊደሎችን ነበር። የመጀመሪያው እትም ነሐሴ 27 ቀን 1968 ዓ.ም የወጣ ሲሆን በዚህ እትም በጋዜጣው ላይ የተጠቀሰው ዋና አዘጋጅ ስም መሀዲ ሀሚድ ሙዴ ይባላል።

የበሪሳ ጋዜጣ እንደጀመረ በመሀል በውል ባልታወቀ ምክንያት ተቋርጦ ነበር። በኋላ በዋና አዘጋጁ ጥረት የካቲት 12 ቀን 1969 ዓ.ም ህትመቱ እንዲቀጥል ሲፈቀድ በጊዜው ከነበረችው ከዛሬቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ጋር በእኩል ደረጃ በስምንት ገጽ በየሳምቱ ሀሙስ 20 ሺህ ቅጅ እንዲታተም ተወሰነ። ይሁንና በጋዜጣው ታሪክ ከፍተኛው መታተም የቻለው ቁጥር 15 ሺህ ቅጅ ነው። በጊዜው ማሽቆልቆል የያዘው በሪሳ ጋዜጣ ህትመት ቁጥር ከ15 ሺህ ወደ 2ሺህ ቅጅ ወርዶ ነበር። ከህዳር 30 ቀን 1985 ዓ.ም ጀምሮ የህትመት መጠኑ ወደ 5ሺህ ቅጅ ከፍ እንዲል እና ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ በባህል እና ኢንፎርሜሽን ሚኒስቴር ስር እንዲካተት የተደረገው በሪሳ ጋዜጣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በአማርኛ ፊደላት መታተሙ ቀርቶ በቁቤ (በላቲን ፊድሎች) እንዲጻፍ እና እንዲታተም ተደርጓል።


የአማርኛ ፊደላት በመጠቀም ሲታተም የነበረ በሪሳ ጋዜጣ


የበሪሳ ጋዜጣ መስራቹ መሀዲ ሃሚድ እኒህ ነበሩ።



ኋላ ላይ በላቲን ፊደል /ቁቤ መታተም የጀመረው በሪሳ ጋዜጣ

## 1.2.9. የግል ጋዜጣ ውልደት እና ሂደት በኢትዮጵያ

በቀዳማይ ኃይለስላሴ ዘመን ጋዜጣን በግል ባለቤትነት (አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ባይሆኑም) መያዝ በተሻለ ሁኔታ ተስፋፍቷል፡፡ ይህንንም
በተመለከተ የካቲት 1927 ዓ.ም ጋዜጦችን እና መጻሕፍትን ለማተም የሚያስችል መመሪያ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ በመቀጠል 1934 ዓ.ም እና
1936 ዓ.ም የወጡ አዋጆች፣ በ1948 ዓ.ም የፀደቀው "የተሻሻለው" ሕገ-መንግስት፣ የ1949 ዓ.ም ፍትሀብሄር ህግ፣ 1966 ዓ.ም ረቂቅ
ሕገ-መንግስት እና መጋቢት 1967 ዓ.ም የወጣው አዋጅ የመናገር እና ሀሳብን በነፃነት መግለጽ መብቶችን በይፋ አጽድቀዋል፡፡ ያም ሆኖ ግን
ከተወሰኑ አጋጣሚዎች በስተቀር በአብዛኛው እነዚህ መብቶች በተግባር አልዋሉም፡፡ በዚህም የተነሳ "የግል" የተባሉት ጋዜጦች በመንግስት
ከተያዙት ጋዜጦች ጋር የነበራቸው ልዩነት አነስተኛ ነበር፡፡ ጋዜጦች ከዚህ በፊት ባልታየ ነፃነት የሰሩበትNA የስርዓቱን ጉድለቶች በግልጽ እና
በድፍረት መጥቀስ እና መውቀስ የቻሉበት ሁኔታዎች ግን በሙሉ አልጠፉም፡፡ የሚጠቀስ ካለም አንደኛው የ1953 ዓ.ም የመንግስት ግልበጣ
ሙከራ በተካሄደ ማግስት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የንጉሱ መንግስት ለመውደቅ በተቃረባቸው መጨረሻ ወቅቶች (1966 ዓ.ም ነበር)፡፡
በወታደራዊ መንግስትም ዘመን በተለይ በአብዮቱ ማግስት በመንግስትም ሆነ የመንግስት ተቃዋሚ በነበሩ ድርጅቶች ባለቤትነት ይወጡ
የነበሩት እነ "ዲሞክራሲያ"፣ "ላብአደር"፣ "የሰፊው ህዝብ ድምጽ" ወይም "ጎህ" በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት የሚካሄድባቸው
መድረክ መሆን ችለው ነበር፡፡ ይህ ነጻነት ግን የቆየው ለአጭር ጊዜ ነበር፡፡ የደርግ መንግስት ማንኛውም የተለየ ሀሳብ ያራምዱ የነበሩ ጋዜጦችን
በመውረስ እና አዳዲሶችን እንዳይጀመሩ በመከልከል የመናገርና አማራጭ ሀሳቦችን በነጻነት የማንሸራሸር መብቶችን ሙሉ በሙሉ አግዷል፡፡
ሥርዓቱ የግል ጋዜጣ መመስረትን በተመለከተም ምንም አይነት አዋጅ አላወጣም፡፡
በሀገራችን መንግስታዊ ልሳን ያልሆኑ የግል ጋዜጦች የተስፋፉት የ1983ቱን የመንግት ለውጥ ተከትሎ ነው፡፡ በ1985 ዓ.ም የወጣው የፕሬስ
ሕግ (የፕሬስ ሕግ 34 /1985 ) በኢትዮጵያ የግል ጋዜጣ ዘርፍ የመሰረት ድንጋይ የጣለ እርምጃ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በአጠቃላይ 1984
ዓ.ም በኋላ የተፈጠረው በኢትዮጵያ የግሉ ጋዜጣ ዘርፍ (ዘርፉ የነበሩበት ውስጣዊ ችግሮችና ውስንነቶች እንዲሁም ከመንግስት በኩል የነበሩበት
ጫናዎች ሁሉ እንደ ተጠበቁ ሆኖ) አንገብጋቢ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ በድፍረት የሚዘገብበትና የሀሳብ ሙግት የሚደረግበት መድረክ ሆኖ
ቆይቷል፡፡ የስልጣን መባለግን፣ ፖለቲካዊ አድልኦን፣ የህዝብ ግጭትን እና ሙስናን በመቃወም በአንፃሩም የመጻፍ ነጻትን፣ የሰብአዊ መብት
ጥሰቶችን፣ የፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ፍትህን፣ ብሄራዊ አንድነት ወዘተ በመደገፍ የተፃፉ ስራዎችን በስፋት አንሸራሽሯል፡፡ በአጭሩ በሀገሪቱ ውስጥ
ሰላማዊ የሆነ የውይይት ባህል እንዲፈጠር ወይም እንዲሰርጽ የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

ከዚህ ገጽ ቀጥሎ የምንመለከተው በኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት አገልግሎት በህትመተ ኢትዮጵያ (Legal Deposit)ክምችት ክፍል የሚገኙ የጋዜጦችን ስብስብ ነው፡፡

-በዚህ ክፍል 1906ከታተመው አእምሮ ጀምሮ በነገሥታቱ ዘመን ለህትመት የዋሉ ጋዜጦች

-በደርግ ዘመን ለህትመት የዋሉ ጋዜጦች

-በኢህአዴግ ዘመን የታተሙ ጋዜጦች

-በተለያየ ዘመን የታተሙ የሐይማኖት፣የስፖርት፣ የፖለቲካ እና የመዝናኛ ጋዜጦችን በከፊል እናያለን፡፡

# በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጋዜጣ ከ1906 ዓ.ም እስከ 1927 ዓ.ም



አእምሮ

AYMERO

PREMIER JOURNAL ETHIOPIEN



አእምሮ

AYMERO

PREMIER JOURNAL ETHIOPIEN

# የኤርትራ ድምጽ

ይህ ጋዜጣ በአጼ ሀ/ስላሴ ጊዜ ኤርትራን በተመለከተ ይወጣ የነበረ ጋዜጣ ሲሆን አገልግሎት እየሰጠ የቆየበትም ግዜ ከ1937 እስከ 1944 ዓ.ም ነበር።


የኤርትራ፡ድምፅ።


የኤርትራ፡ድምፅ።

# ጃንሆይ፡በመንግሥታት፡ማኅበር፡

[illegible]



# የማይጠፉ፡ምርኮኞች፡

[illegible]



[illegible]

# በሪሳ / BARIISSA/ ጋዜጣ

በሪሳ ጋዜጣ የመጀመሪያው በኦሮምኛ ቋንቋ የታተመ ጋዜጣ ሲሆን በአገልግሎት ላይ የቆየበት ጊዜም ከ1969 ዓ.ም እስከ 1979 ዓ.ም ድረስ ነበር።



Bariisaa

"Har'as Boris Teessoon Keenya Finfinnee dha"

Gaazexeessitotni Waldaan Kurfaa'an

Karoora Yaadamee of Horate

Maree Koree Dhimmaa Dubartoota Oromiyaa



በሪሳ

# የዛሬይቱ ኢትዮጵያ

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ በቀዳማዊ  ኃይለ ስላሴ ዘመን ጀምሮ እስከ ደርግ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ድረስ የቆየ ጋዜጣ ሲሆን ከ1945 እስከ 1969 ዓ.ም አገልግሎት ላይ ውሎ ነበር ።


L'ETHIOPIE D'AUJOURD'HUI

Négociations économiques entre l'Éthiopie et Israël

BARRAGES

La récolte éthiopienne de café 1957

ème Compétition d'Athlétisme


L'ETHIOPIE D'AUJOURD'HUI

Le premier vol Addis-Abeba-Francfort

Audiences

# የኢትዮጵያ ድምጽ

የኢትዮጵያ ድምጽ ጋዜጣ በአጼ ኃይለስላሴ ዘመን ጀምሮ እስከ ደርግ መጀመሪያ አካባቢ ይወጣ የነበረ ጋዜጣ ሲሆን በአገልግሎት ላይ የቆየበት ግዜም ከ1945 ዓ.ም እስከ 1969 ዓ.ም ነበር።



የኢትዮጵያ፡ድምፅ

አዲሱ ዓመትና ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተዋሐደችበት በዓል ተከበረ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የሰጡት መልስ

የኢታንት ፕሮግራም ለኮንጐ ባለሥልጣኖች ተላከ

በአልጄሪያ ሰላምና ጸጥታ ተመለሰ

ሎተሪ

የኮመንዌልዝ አገሮች በኤሮፓ የጋራ ገበያ ውስጥ ያላቸው አቋም



የኢትዮጵያ፡ድምፅ

በኢትዮጵያ የመኪና ንግድና ነጂ ቁጥር እየቀጠለ ይሔዳል

የልዩ ኮርስ ፈተና ውጤት

ቤን ኬህዳ ከእጩነት መዝገብ ተሰረዙ

የማዕከላዊ ኮንጎ መንግሥት ሊወጋን ይዘጋጃል -ቾምቤ

50,000 ግራኮች በመውጣት ላይ ይገኛሉ

ኬኔዲ ለኮንግረስ የአቀረቡት አሳብ ተፈቀደ

# ሰንደቅ ዓላማችን

ሰንደቅ ዓላማችን ጋዜጣ ልክ እንደ ሮማ ብርሃን ወይም የቄሳር መልዕክተኛ ጋዜጣ ጣልያን ኢትዮጵያን በተቆጣጠረበት ግዜ ይወጡ ከነበሩት ጋዜጦች አንዱ ሲሆን በአገልግሎት የቆየበት ግዜም ከ1934ዓ.ም እስከ 1941 ዓ.ም ነበር ::







ሰንደቅ፡ዓላማችን


ሰንደቅ፡ዓላማችን

# የቄሳር መልዕክተኛ

ጣሊያን ኢትዮጵያን በተቆጣጠረበት ጊዜ እና ዘመን ይወጣ የነበረው ጋዜጣ ሮማ ብርሃን ወይም የቄሳር መልክተኛ ይህን ይመስላል። የቆየበትም ግዜ ከ1934 ዓ.ም እስከ 1941 እ.ኤ.አ ነበር።


የቄሣር፡መንግሥት፡መልክተኛ።

የኢጣሊያ፡የጦር፡መርከቦችና፡አኤሮፕላኖች፡በሜዲቴራኔዮ፡ባሕር፡ በእንግሊዝ፡ላይ፡ታላቅ፡የሆነ፡የድል፡አድራጊነት፡ሥራ፡ሠሩ።


የቄሣር፡መንግሥት፡መልክተኛ።

ጄኔራሌ፡ናዚ፡በሱማሌ፡አገር፡ስላደረገው፡ታላቅ፡ድል፡የአዲስ፡አበባ፡ሕዝብ፡ታማኝነቱንና፡ደስታውን፡ገለጠላቸው።

## 2.2 የ “አዲሱ ዘመን” ጋዜጦች

# አዲስ ዘመን

አዲስ ዘመን ጋዜጣ ከ 1933ዓ.ም በኋላ በአጼ ሀ/ስላሴ ዘመን ጀምሮ እስካሁን አገልግሎት እየሰጠ ያለ ጋዜጣ ነው።



አዲስ ዘመን

አቶ መለስ ዜናዊ በሀገራችን የነበረው ጦርነት እንደማያገረሽ አረጋገጡ

የጐንደር ከተማ ሕዝብ በሰላማዊ ሰልፍ ለኢሕአዴግ ድጋፉን ገለጠ

ፕሬዚዳንት መለስ መልዕክት ላኩ

የፈላሾች መኘተ ኢ-ሰብአዊና አሳፋሪ ድርጊት መሆኑ ተገለጠ

ለገሰራና ሆራ አሩሬጂ ሕዝብ ገለፃ ተደረገ

አሜሪካ ለቀድሞ መንግሥት ወታደሮች ርዳታ ላከች

የቀድሞ ባለሥልጣናት እጃቸውን መስጠት ቀጥለዋል



አዲስ፡ዘመን

የትኛ ግዛቶችን ጉዳይ የሚመረምረው ኮሚቴ ሥራውን ጀመረ

በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ ዶክተር ተስፋዬ ገብረ እግዚእ

በሥራ ላይ የሚውል ጥናት

ዓለምን የሚጐበኙ ሰዎች

የአዲስ አበባ



# አዲስ ዘመን

## ኢኮኖሚውን ማሳደግ - የለውጡ አንዱ ምሰሶ

## በአምቦ ኮርማ ታርዶ በኦሮሚያ ሰላም ታውጇል

### ዘመናዊ የክፍያ ስርዓት - ለተቀላጠፈ አገልግሎት

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት

አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ ADAMA STEEL FACTORY

በፍቅር እንደመር በይቅርታ እንሻገር!



ዕለተ ሰንበት

# አዲስ ዘመን

## የፖለቲካ አመለካከትን በሰላማዊ ውይይት ለመለዋወጥ የሚያግዝ መድረክ ተካሄደ

በውስጥ ገጾች

## ዶክተር ዐቢይ ቤት የገባው ‹‹ሚሊዮን›› ስጦታ

### የጎዳና አበባዎች ፍሬ እንዲያፈሩ

አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ ADAMA STEEL FACTORY

በፍቅር እንደመር በይቅርታ እንሻገር!

ሰርቶ አደር ጋዜጣ በደርግ ዘመን ከፍተኛ ተነባቢነት የነበረው ጋዜጣ ሲሆን የቆየበትም ግዜ ከ1972 ዓ.ም እስከ 1982 ዓ.ም ነበር።


ሠርቶ አደር

የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ልሳን

የኢሠፓአኮ አንደኛ ጉባኤ ውሳኔ

የኢሠፓአኮ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት


ሠርቶ አደር

የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ልሳን

የሰፊው ሕዝብ የማንበብ ልምድ እንዲዳብር

የአብዮታዊት ኢትዮጵያና የላይቤሪያ አዲስ የትግል አንድነት ምዕራፍ



ሠርቶ አደር

የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ልሳን

የሁሉንም ቤት የማንኳኳት ዝንባሌ ያለው ዘመቻ

የአፍሪካ አገሮችን የንግድ ግንኙነት ለማጠናከር



ሠርቶ አደር

የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ልሳን

ከሶሻሊስት ሀገሮች ጋር የመሠረትነው ግንኙነት ፍሬ እያሳየ ነው

በዓለም የመጀመሪያዋ የቤት ጠፈረተኛ ለጉብኝት መጡ

ለታዳጊ ሀገሮች ትኩረት እንደሚሰጥ ተገለጸ

# ታጠቅ ጋዜጣ

ታጠቅ ጋዜጣ በደርግ ዘመን ይወጣ የነበረ ጋዜጣ ሲሆን በአገልግሎት ላይ የቆየበት ግዜ ከመስከረም 1972 ዓ.ም እስከ ነሃሴ 1978 ዓ.ም ነበር።



ታጠቅ

የአብዮታዊት ኢትዮጵያ አብዮታዊ ጦር ጋዜጣ

## በአብዮታዊ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ሴሚናር ተካሄደ

## የ6ኛው አብዮት በዓል የሠልፍ አሸናፊዎች ተሸለሙ

## ዚያድ ባሬ ያፈናቀላቸውን ጉዳተኞች ለወታደርነት እየመለመለ ነው

በውስጥ ገጾች



ታጠቅ

የአብዮታዊት ኢትዮጵያ አብዮታዊ ጦር ጋዜጣ

## ጓድ ሊቀ መንበር ጉብኝታቸውን ፈጽመው ተመለሱ

## የዚያድ ባሬ ውጥረት !

የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያንና የሶቪዬት ኅብረትን የጋራ መግለጫ ሙሉ ቃል በ6ኛው ገጽ ይመለከቱት

በውስጥ ገጾች



ታጠቅ

የአብዮታዊት ኢትዮጵያ
ጦር ኃይሎች ጋዜጣ

# አብዮታዊው ሠራዊታችን ለቀረው ትግልና ድል ያለውን ብቃትና አብዮታዊ ዲሲፕሊን በደማቅ ሠልፍና በልዩ ልዩ ወታደራዊ ትርኢቶች ያሣያል

ርዕሰ አንቀጽ

## ለማያቋርጠው ትግል መዘጋጀት

አብዮታዊው ሠራዊታችን

## አምስት የመሥዋዕትነት ዓመታት



ታጠቅ

የአብዮታዊት ኢትዮጵያ
ጦር ኃይሎች ጋዜጣ

# የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ከፍተኛ ሹመትና የማዕርግ ዕድገት ሰጠ

በትርቡ የተሾሙት የሀገር መከላከያ ሚኒስትር

## አዲሱን ሥራቸውን ተረከቡ

## አብዮታዊው ሠራዊት የሚያደርገው የገንዘብና የጉልበት አስተዋፅኦ ቀጥሏል

# ፖሊስና እርምጃው

ፖሊስና እርምጃው ለረዥም ጊዜ እየታተመ ሲነበብ የኖረ ጋዜጣ ነው።



ፖሊስና·እርምጃው

በጭስ ታፍነው ሞቱ

ዕድገት አገኘ

ማጅራት መቺዎች ተያዙ

ገዳይ ነህ እባላለሁ



ፖሊስና·እርምጃው

ደጃዝማች አሉላና ግብረ አበሮቻቸው ፍርድ ቤት ቀረቡ

የሀሰት ሪፖርት ያቀረቡ ፖሊሶች ግርፋት ተፈረደባቸው

ሚስት ባለማግባቱ የአባቱን ቤት አቃጠለ?

# ዘመነ-ኢህአዴግ

በ1983 ዓ.ም የደርግ መንግስትን መውደቅ ተከትሎ ስልጣን የያዘው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) አስተዳደር ከዚያ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በርካታ የግል ጋዜጦችና መጽሔቶች እየታተሙ ይሰራጩበት የነበረ ዘመን ነበር። በዚህ ዘመን ቀድመው የነበሩትና የመንግስታት ልሳናት ሆነው ያገለግሉ የነበሩት ጋዜጦች ያንኑ ሥራቸውን የቀጠሉ ሲሆን የተለያዩ የፓርቲና የክልል መንግስታት ልሳናት ሆነው የሚያገለግሉ ጋዜጦችም ተቋቁመዋል። ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ፎቶዎች ደግሞ ከ 1983 ዓ.ም በኋላ የወጡ የግል ጋዜጦች ሲሆኑ ፖለቲካዊ፤ መዝናኛ፤ ሃይማኖታዊ ስፖርት እንዲሁም ጤና ነክ ጉዳዮችን ይዳስሳሉ።

# አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋዜጣ

የመጀመሪያው የኢሕአዴግ ልሳን ጋዜጣ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሲሆን ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2004 ዓ.ም አገልግሎት እየሰጠ የቆየ ጋዜጣ ነበር።


አብዮታዊ ዴሞክራሲ
የኢህአዴግ ልሳን
ዋጋ 50 ሣ
ህዝቡ የመረጣቸውን አስተዳዳሪዎች ገመገመ
"ክርስቶስን ብሆን-ሰማይና ምድርን በአንዲት ደቂቃ ሸብልያት ነበር"
-አባ አምሀየስ
"በሁለት ቢላ መብላት ተገቢ አይደለም"
በዚህ እትም

# አብዮታዊ ዴሞክራሲ

## 120 ታዛቢዎች ለኤርትራ ውሳኔ ሕዝብ

## ሞሶሊኒ ሥልጣን የጨበጠበት 70ኛ ዓመት ተከበረ

## የሥራ ዘመቻ ተካሄደ

## በሐረር የተዘጉ ሐኪም ቤቶች ተከፈቱ

## ፖሊስ ስብሰባ አካሄደ

## 300ሺ ሰዎች ተሰደዱ

## በድንገቱ የማስተማር ሥልጠና የተከታተሉ ተመረቁ

በዚህ እትም

# አብዮታዊ ዴሞክራሲ

## በአርባ ጉጉ ኦሮሞዎችና አማሮች «ባንድነት መኖሩን እናቅበታለን!» አሉ

## ከባእድ አገር ወደ ትውልድ መንደር

## በእንግሊዝ ሠራተኞች ወደ አመጽ እያመሩ ነው



## ራሽያ የ22 ቢሊዮን ዶላር እርዳታ ትሻለች

## ከ19 ዓመት በኋላ ወግ ደረሰው

በዚህ እትም


አውራምባ ታይምስ
በመረጃ ቅርብ ይሁኑ
በግንቦት 7 የተከሰሱት እነማን ናቸው?
የነጻነትና የአዲስ ዜና ጋዜጣ አዘጋጆች በክሱ ውስጥ ተካተዋል
8


ጄኔራል ተፈራ ማሞ የተባሉት ሰው አጭር ይሁኑ ረጅም፣ ቀጭን ይሁኑ ወፍራም አላውቅም። አቶ መሳይ ተፈራ የተባለውንም በሕይወቴ አይቼው አላውቅም
ስኬት
SUCCESS

# ኢትዮ ቻናል ጋዜጣ



ኢትዮ ቻናል

«እናቴ አቅም ካለህ ይህችን አገር እንድትረዳ ብላኛለች»

ዶ/ር ሼኽ መሐመድ ሁሴን አልአሙዲ

③

«ኢትዮጵያ የተቀደሰች አገር ናት» ④

ካሚላት ለአዲሱ ዓመት ወደ ሃገርዋ መጣች ④



እንግዳ

# ኢትዮ ቻናል ጋዜጣ



ኢትዮ ቻናል

የምንፈራው ውሸትን ብቻ ነው!!

«የኤርትራ ሰራዊት በአሁኑ ሰዓት የአንድ ጥይት ጩኸት ብቻ እየጠበቀ ነው»

«ኤርምጃው ለአሜሪካም ሆነ ለኢትዮጵያ ፍላጎት አይጠቅምም»

«የኢትዮጵያ ህዝብ የአሜሪካንን ድጋፍ የሚፈልግበት ወቅት ላይ ነን»

ታዋቂው የ CNN ጋዜጠኛ ላሪ ኪንግ 7 ሚስቶችን ተፋቷል

«ብጃፓን የጠፉት 3 ጋዜጠኞች ለጥገኝነት ሲሉ የአገርን ስም አጥፍተዋል»



እንግዳ

«የኢሳያስ አፈወርቂ መጨረሻ እንደ ሳዳም ሁሴን እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ»

# ምኒልክ ጋዜጣ



ምኒልክ

«በትግራይ ሆቴል ፍንዳታ ሳቢያ በርካታ ኦሮሞዎች እየታሰሩ ነው»

«ቢጋምቤላ የቦምብ ጥቃት ተፈፀመ፣ 5 ሰዎች ሞቱ» I.R.I.N.

«ፍንዳታውን ከኦነግ ለማያያዝ እየተሞከረ ነው»ኦ.ነ.ግ

«አሁብ ይመስስ ማስታቸው አይገርምም»

የኤርትራው ፓትርያርክ ሬሲጾስ አረፉ



ምኒልክ

D.V. 2004

«የአዲስ አበባ አስተዳደር /ዓሊ አብዶ/ ብቃት የለውም፣መንሳት አለበት» አባይ ፀሐዬ

ዓሊ አብዶ በአደባባይ ተብጠለጠሉ

«በአዲስ አበባ 10 ማዘጋጃ ቤቶች ይኖራሉ»

«የኦ.ነ.ግ ጦር እርስ በእርሱ እየተዋጋ ነው»

ያለመከሰስ መብታቸውን የተገፈፉ የፓርላማ አባላት 20 ደረሱ

# ሰንደቅ ጋዜጣ


ሰንደቅ
«የሚያስፈልገው የእልህ ሳይሆን
የመቻቻልና የድርድር ፖለቲካ ነው»
ምርጫ ቦርድ ኢህአዴግ 296 ቅንጅት 109
ኅብረት 52 መቀመጫዎች ማሸነፋቸውን ገለፀ
አቶ ልደቱ አያሌው
መግለጫ ላለመስጠት ወሰኑ
ቅንጅት በሶማሌ ክልል ምርጫ
እንደሚያሸንፍ ገለፀ
የቻይና ኮሚዩኒስት ፓርቲ
በኢህአዴግ አሸናፊነት መደሰቱን ገለፀ


ፖለቲካ
ሠላም የሚጠቅመው
በቅድሚያ ሕዝብን ነው

# ኢትዮጲስ ጋዜጣ

ኢትዮጲስ ጋዜጣ በታዋቂው የመብት ተሟጋች እና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ የሚታተም ጋዜጣ ሲሆን በ2011 ዓ.ም ገበያ ላይ መዋል ችሎ ነበር። ከ2013 ዓ.ም ወዲህ ግን ከገበያ ጠፍቷል።



ኢትዮጲስ

የንፁሃን ደም ይጮሃል... ፍትህ! ፍትህ!ፍትህ!

ግድያ፣ ሰቆቃ፣ መፈናቀል ... በቡራዩ... አሸዋ ሜዳ ... አዲስ አበባ

ኢ.ህ.ዴ.ድ 14 ነባር አመራሮችን አሰናበተ



የጌታቸው አሰፋ ስውር እጆችና ብሔራዊ አደጋው

# አውራምባ ታይምስ



አውራምባ ታይምስ

ቴዲ አፍሮ ጥፋተኛ ተባለ

«እግዚአብሔር ይፈርዳል» ቴዲ

ቤተሰቦች እና አድናቂዎች በእምባ ተራጩ

«ከእንግዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃ ምርጫ ይኖራል ብዬ አላምንም»

ድምጻዊ ቀመር የሱፍ ተቃውሞ ገጠመው



አውራምባ ታይምስ

«ስካይ ባስ የሁሉም ነው»

«ፖለቲከኛው ታምራት የክርስቶስ አገልጋይ ሆነ ብለህ ብትፅፍ ደስ ይለኛል»

Awramba Exclusive

ሁለት ባለሀብቶች በአንድ ሳምንት እራሳቸውን አጠፉ

«ጫማው ቀርቶብኝ ጥያቄ በወረወርኩ»

የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔና የኢትዮጵያ ከሶማሊያ ለቆ መውጣት



አፎይታ

ቅልጥፍና ኢንቬስተሮችን ወደ ትግራይ እየሳበ ነው

ሥራ ለ200ሺ. ዜጎች

አዋላጅዋ ፅንሱን በጩቤ ዘለዘለች

ሱዳን ኢትዮጵያን ለመቀረስ ማሰብዋ ተጋለጠ

የፎረም 84 ንብረት እየተዘረፈ ነው



ገድል

ከጣርማ በር

«ውጊያው ያለቀው ከግንቦት 20 በፊት ነው»

ገድል

እስከ አዲስ አበባ

# እፎይታ ጋዜጣ



እፎይታ

ቁጥር 75 … ሐምሌ 1/1990 … ዋጋው 1 ብር

«ተረኛ ነኝና እንዳትሸበሪ፣ ስለይሽ አዝናለሁ እናት ደህና እደሪ»



እፎይታ

ቁጥር 68 … ግንቦት 12/1990 … ዋጋው 1 ብር

ወራሪው የኤርትራ ጦር ይዞታውን እያጠናከረ ነው

ክልላዊ መንግስታት የኤርትራን ወረራ ለመመከት ዝግጁነታቸውን አረጋገጡ

ዶ/ር ነጋሶ «ማንም ከማንም አይበልጥም» ሲሉ አስታወቁ

የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን (ኢ.ቴ.ኮ)

የሞባይል አገልግሎት ምዝገባ ማስታወቂያ


ስፖርት ኢትዮ ኒውስ
ፕሪምየር ሊጉ ተሟሟቀ
ቅ/ጊዮርጊስ 4 መድን 0
ሙገር 1 ቡና 4
መብራት ኃይል 2 ኒያላ 1
ማይክ ታይሰንና ልዊስ ሌኖክስ ፕሬስ ኮንፈረንስ ላይ ተደባደቡ
ቅ/ጊዮርጊስ እና አሸናፊ ፊት ለፊት ሊወያዩ ነው
ኢትዮ ኒውስ
«አላማህን ለማሳካት ስትጓዝ መሰናክል አታጣም»
የአሜሪካ ኢምባሲ ዲፕሎማት ሰው ገደሉ
«እኛ ኢትዮጵያውያን እንጂ አሜሪካውያን አይደለንም»


ኢትዮ ኒውስ
«ጉች ጉች» ያለ ጡት ናፍቆኛል
ቀልብ የሳበው የቴአትር ቤቶች ውድድር
ወሲባዊ እርቅ

# ሳተናው ጋዜጣ



ሳተናው

አስኳል

የማክሰኞ ጋዜጣዎ

«የመለስ ዜናዊ ባለቤትን አግደናል»

«የታገዱት በመጥፎ ተግባራቸው ነው»

«ያሳገዱኝ እነተወልደ ናቸው»

«የመለስ ባለቤት እንዲባረሩ ወስነናል»

«ተወጠርን»

የመቀሌ ወጣቶች እየታፈሱ ነው

መርካቶ ቦምብ ፈነዳ (ገፅ10)

«ስዬም የራሱ ሃሣብ ኖሮት አያውቅም»እነስዬ

በሕወሃት ኮንፍረንስ



ሳተናው

ታሪክ ስሩ

«ትግራይን ማየት ማመን ነው»

አልማዝ መኮ (ቃለምልልስ)

6 ሊቀ ጳጳሳት ተቃውሞ አነሱ

«...ጠጪ ነኝ...» ስብሃት ነጋ

«መንግሥት ቃሉን አጥፏል»

«መለስ አግልለውኝ ነበር» አርከበ እቁባይ

«አልማዝ የከዱት በምዕራብ ዓለም ለመኖር ሲሉ ነው»

«አህዴድ ሲፋቅ አነግ ነው»



ሳተናው

ሣይንስና ቴክኖሎጂ

# በቀን ስምንት ሰዓት እንቅልፍ ያስፈልገናል

# «በአሜሪካ የብር ኖቶች ላይ የአደገኛ ዕፆች ብናኝ በብዛት ይገኛል»



# «ዝምድናና ጋብቻ የግድ መነጣጠል የለባቸውም»



ሳተናው

ዓርብ ማለዳ

ዕለ ዘገባ

አሰብ ደህና ሁኚ!

# «የዛላንበሳ ግማሽ ለኤርትራ ተሰጥቷል»ሻዕቢያ

የባድመ ትይዩዎቹ ሸሸቢት፣ ሽላሎና ትኮምቢያ ለኤርትራ ፀንተዋል

# አዲሱ ካርታ በኤርትራ ቴሌቪዥን ይፋ ሆነ

Ethiopia Loses Badme and Tsorona to Eritrea but Eritrean agents in Addis Ababa confuse Ethiopian people who nonetheless have rejected the deal altogether



«ደህንነት መረጃ ደርሶታል»

# ኦህዴድ ዳግም ተከፋፈለ

B.B.C. FOCUS ON

«ኢትዮጵያ በአካባቢው ኃያል ሆናለች»

# ሴት

## የመጀመሪያዋ ሴት ሚኒስትር ሩጫቸውን ጨረሱ



### አስራ ስምንት ወራት ወንድ ሆና የኖረችው ሴት





### ደህንን ያውቃ ናሯል?

## የቅንጅት አመራሮች... የፍርድ ቤት ውሎ



# በኩር ጋዜጣ

በኩር ጋዜጣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሚታተም ሳምንታዊ ጋዜጣ ነው።


በኩር

የአገው አዊ ሕዝብ ቋንቋ ወደ ጽሁፍ ቋንቋ በሚሸጋገርበት ሁኔታ ውይይት ተካሄደ


ጥበብ

ከሰማይ የተገኘ ፍርድ

አጭር ልብ ወለድ

# አቆልቋይ

# ዓውደ ባህል





ከአብኮመ ጤና ግብቃ ቢሮ ጋር በመተባበር የቀረበ

# "ህዳር ሲታጠን ..."





## ለጤናዎ ዜናዎች

### ማህበራዊ ድረ ገፆች ወጣቱን ከኤች አይ ቪ ለማጋለጥ ሚና አላቸው

### ነዋሪዎች የፎከት በሽታ መድኃኒት ተጠቃሚ ሆኑ

# አእምሮ ጋዜጣ



አእምሮ

«የሰላምና እርቅ ጉባኤ በአዲስ አበባ መደረጉ አይቀሬ ነው»ተባለ

«ኢትዮጵያውያን ከሀብታቸው ባሻገር ህልውናቸው እየተፈረደበት ነው»

መድህን ፓርቲ የትጥቅ ትግል ለመጀመር ወሰነ

የኢህአዴግ ተፋላሚዎች የተኩስ አቁም ስምምነት ተጠየቀ

«የኢትዮጵያህዝብያሸንፋልየትግራይ ህዝብ ለዳግም ታሪክ ይዘጋጃል»

የመአህድና የቤተ ክህነት መግለጫዎችህዝብእያነጋገሩነው

የ42 ምሁራንና የዩኒቨርሲቲው ፍጥጫ ተጀመረ

ህገ መንግሥቱን ህዝቡ በዝምታ የተቃወመው ይመስላል

በስደት በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ ግድያ ተፈፀመ



አእምሮ

በኤርትራ 11ኛ ክፍል መፈፀም ከኢትዮጵያ 2ኛ ደረጃ ማጠናቀቅ ጋር ተመጣጣኝ ነው ተባለ

ኢህአዴግ የእርቀ ሰላሙን ዝግ ውይይት ድምፅበምስጢር መቅዳቱ ታወቀ

አቶ ጌታቸው ይግዛው አረፉ

የሠንዳፋው የጦር ክምችት በምስጢር ተጎበኘ

የህገ መንግስቱ ውይይት ያለ ህዝብ ተሳትፎ እየተከናወነ ነው

ከሥራ ታገዱ የተባሉት ሹም አለመታገዳቸው ታወቀ



# ዕለታዊ አዲስ

«ድርጅታችን ሰፊ ልምድና ብቃት ያለው ነው» ኢህአዴግ

## «የሌሎች ፓርቲ አማራጮችን አለማየት የኢህአዴግ ትልቁ ድክመት ነው» ኢዴፓ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

የቅድስት አንበሳ ሆስፒታል በዘውዲቱ ሆስፒታል ስም

አዲስ የጀመረውን በፅሁፍ ፕሮግራም የማስተዋወቅ ዘዴ እንዲቀይር ዓይነ ሥውራን ጠየቁ

በሀሺሽ ንግድ

ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅትና

ማስታወቂያ

የመረጃ ልውውጥ ለንግድ እንቅስቃሴ መሠረት ነው



# ዕለታዊ አዲስ

ፖለቲካ - ኢኮኖሚ - ማህበረሰብ

## «...አሰብ የአፋር ነው፡፡ አፋር ደግሞ የኢትዮጵያ ነው...»

«በርካታ ሴቶች፣ አግብተቻቸው ውጪ የሚወስዳቸው ባል ይፈልጋሉ»

ትላልቅ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ለሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች በመስጠት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማዳን ይቻላል

# ሪፖርተር ጋዜጣ



ሪፖርተር

FREE PRESS FREE SPEECH FREE SPIRIT

## የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የተቃውሞ ሰልፍ ተበተነ

## በአቶ ታምራት ላይ የሚሰጠው ፍርድ ይግባኝ አይኖረውም

## የቤተክህነትን የኪራይ ተመን ለመክፈል ያልቻሉ ተከራዮች እየለቀቁ ነው

. ማህበር ሊያቋቁሙ ነው

## የሱዳን መንግሥት ተቃዋሚ ኃይሎች የማጥቃት እርምጃቸውን አጠናከሩ


ለተሻለ ዋጋ
በተሻለ ፍጥነት
በቀላል ጉዞ
የተሻለ
የጉዞ ወኪል

የዘመኑ
ምርጥ ቢራ
በደሌ ቢራ
BEDELE BEER
THE BEER OF THE DAY

TDS
የሕፃናትና የእናቶች
ልብስ መሸጫ
TDS

ዋቢ ሸበሌ
ሆቴል
ዋቢ




## ...በረራ

Boeing 767

## ኮሞሮስ

# የሐይማኖት ጋዜጦች

የእምነት ተቋማት /ከተለያዩ እምነቶች ጋር ግንኙነት የነበራቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች ከ1983 በኋላ የተገኘውን ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ /የማራመድ ነጻነት ተጠቅመው የየራሳቸውን ጋዜጣና መጽሔት በማሳተም ምዕመናትን ማስተማርና የሚከተሉትን እምነት ሀሳብ በሰፊው ያንጸባርቁ ነበር።

## ዜና ቤተክርስቲያን ዘኢትዮጵያ ጋዜጣ



ዜና ፡ ቤተ ክርስቲያን

ዘኢትዮጵያ

መናፍቁ ጳጳስ ተወግዞ ተለየ



ዜና፡ቤተ ክርስቲያን

ዘኢትዮጵያ

እንኳን ከዘመነ ማቴዎስ ወደ ዘመነ ማርቆስ አሸጋገረዎ

# የእስልምና ሃይማኖት ጋዜጣ

## ኢትዮ ሙስሊም ጋዜጣ



ኢትዮ ሙስሊም

The Name of Allah

ቅጽ 001 ቁጥር 003 መስከረም 21/2003 ዋጋ 3.00 ብር

ለቅዱስ ቁርዐን

የሰሀራ በረሀን በእግር ያቋረጡ

ኢትዮጵያዊ

ሐጅ በ36,200 ብር

1,200 ሐጃጆች ተመዝግበዋል

ቀድሞ የተመዘገበ ቀድሞ ይጓዛል

ለሐጅ ጉዞ መሳካት የተባበሩ ይሸለማሉ

በፌዴራል ጉዳዮች ሚ/ር የኃይማኖትና እምነት ዳይሬክቶሬት ለሚዲያ ባለሞያዎች የተዘጋጀ የግንዛቤ ማስጨበጫ ወርክሾፕ ላይ ጋዜጠኞች በኃይማኖቶች ጉዳይ ተወያዩ

ለበኒ ንናቄራ መስጅድ የበኩሉን ያደረገ ሸህ



ኢትዮ ሙስሊም

«የነብያችንን /ሰዐወ/ ደብዳቤ እናስመጣለን»

ገጽ 3

«የዘንድሮው የሐጅ ጉዞ መስተንግዶ ማዕከላዊነት ባለው መልክ በየክልሎች ምዝገባ እየተካሄደ ነው»

የሳውዲ ዶክተሮች የሸሪያ ስልጠና እየሰጡ ነው

በዋሺንግተን ኢትዮጵያዊያን የመጀመሪያውን

ታላላቅ የሳውዲ ዑለማዎች አሕመዲል ነጃሺን ዘየሩ

ዜናዎቹን በውስጥ ገጽ ይመልከቱ

# ሂጅራ ጋዜጣ



بسم الله الرحمن الرحيم

ሂጅራ

በውስጥ ገጾች...
- የምላስ ጣጣ
- ሁለት ልቦችን...
- የኢስላም ሸሪዓ...
- ኢስላማዊ...

## የሸኽ ዛይድ ቢን ሱልጣን መስጊድ ተመረቀ

### በአይነቱ ዘመናዊ የሆነ ኢስላማዊ የባህል ማዕከልም ሊቋቋም ነው

### አረብ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖችን ወደ ውይይት የሚያመጣ ስምምነት ተፈረመ

### የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሙስሊም ተመራቂዎች የመሸኛ ዝግጅት አካሄዱ

### የአሜሪካ የሃይማኖት ነፃነት ኮሚሽን ከአል አዝሀር ኢማም ጋር ተወያዩ



بسم الله الرحمن الرحيم

ሂጅራ

በውስጥ ገጾች...
- ሰብአዊ
- እያነሱ እስከሰታ
- ሙሐመድ የኢስላም ነብይ
- ሚሊኒየም የኛ
- ኤች.አይ.ቪ

## 3ኛው አለማቀፍ የሙስሊም መሪዎች ኮንፈረንስ በአዲስ አበባ ሊካሄድ ነው

### ክርስቲያን ሴቶች ለሂጃብ ያላቸውን ክበሬታ ገለፁ

### መጅሊሱ ሚሊኒየሙን ለማክበር ዝግጅት እያደረገ ነው

# የስፖርት ጋዜጦች

## መርሐ ስፖርት

መርሐ ስፖርት ጋዜጣ የመጀመሪያው ሙሉ በሙሉ ስፖርታዊ ጉዳዮች ላይ የታኮረ የስፖርት ጋዜጣ ነው፡፡



መርሐ ስፖርት

የሐረርጌ ሻምፒዮና በአጋዴን አንበሳ የበላይነት ተፈጸመ

የአዲስ አበባ ስፖርት ም/ቤት ዓመታዊ ውድድሩን እያካሄደ ነው



በብሔራዊ ፌዴሬሽኖች

ብሔራዊ ፌዴሬሽኖች በ1970 ዓ.ም. ምን ሠሩ !

# ሊብሮ ጋዜጣ

ሊብሮ ጋዜጣ በታዋቂው ጋዜጠኛ ገነነ መኩሪያ አዘጋጅነት ሲወጣ የነበረ ተወዳጅ ጋዜጣ ነበር።



ሊብሮ

15ኛው የአለም ዋንጫ ከምድብ ለማለፍ የመጨረሻ ደረጃ ላይ ደርሷል

በፖለቲካ የታመሰችው ናይጀሪያ በኳስ ሜዳ እያመሰች ነው

ተከላካዩ የተማሠረው በቃል ኪዳን በንበሰት ነው ተባለ

የፕላኔቶች ውድድር ቢኖር ብራዚል መሬትን ወክላ ትሠለፋለች



ሊብሮ

ከካይሮ መልስ ወጣት ቡድናችን ዛምቢያን ለመጀመሪያ ጊዜ ነገ ይገጥማል

ኤሌትሪክ በሲሳይ ላይ ያወሰነውን የቅጣት ውሳኔ ፌደሬሽኑ ሻረው

# ኢንተር - ስፖርት


ኢንተር-ስፖርት


ኢንተር-ስፖርት

# ኢትዮ-ስፖርት



ኢትዮ-ስፖርት

227

የእሁዱ ተዓምር!

4-0

ዳዊት! ዳዊት! ዳዊት!

OPSUN P.L.C.

Satellite Dish Sales & Installation



ኢትዮ-ስፖርት

197

ድርብርብ ወርቆች

OPSUN P.L.C.

# እውነተኛ ፍቅር ጋዜጣ

የ1983ቱን የመንግስት መለወጥ ተከትሎ እንደ አሸን ፈልተው ከነበሩ የግል ጋዜጦች መካከል ትኩረታቸውን ሙሉ-በሙሉ በመዝናኛ ኢንዱስትሪው ላይ ብቻ ያደረጉ ጋዜጦችና መጽሔቶች ነበሩ። ከእነዚህም መካከል የእውነተኛ ፍቅርና ኤሮቲካ ጋዜጦችን በዚህ ህትመት ተካተዋል።







# እውነተኛ ፍቅር
True Love

«የሐበሻው የሙዚቃ ንጉሥ» የጥላሁን ገሠሠ 60ኛ ዓመት በድምቀት ተከበረ!!

ሼክ መሐመድ አላሙዲን ለጥላሁን ያላቸውን ልባዊ ፍቅር አረጋገጡ!

"... የጥላሁን ልደት ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም አርቲስቶች ልደት ነው..."

"... ልጄ ጋይልኛ የሙዚቃ አፍቃሪ ናት... ታላቁ የአሜሪካ ቴትሪል ፕሮፌሽናል ተጫዋች ነው..."

"... ወደ ሙዚቃው ዓለም የገባሁት በጥላሁን ዘፈን ተማርኬ ነው..."

ለፍቅረኛዋ ስትል የጉዳና ቤተኛ የሆነችው ገላዬን እንጂ ልቤን አልሸጥም አለች!!

የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሠላም አደረሳችሁ

TRUE LOVE


# ኤሮቲካ

ሊዛ ሜሪ ከማይክል ጃክሰን ጋር ባሳለፈችው ትዳር እንደምትቆጭ ለመጀመሪያ ጊዜ አስታወቀች

ታማኝ በየነ «ቅን ተገዢ መሆኑን» ለኢትዮጵያን ሬጅስተር ገለፀ

ቻቺ ታደሰ ለህጻናት ቤተኛ አዳሪዎች የላትን ድጋፍ እንደምትገፋበት ገለፀች

ሙሉ ካሴቱን ተዘረፍኩ የሚለው ድምጻዊ ሚማዬ አለቀ እንጂ ውሜ አላገኘሁም ሲል አማረረ



# ኤሮቲካ

Tom Cruise & Nicole's sizzling

በኃይሌ ገሪማ ድጋፍ አሜሪካ የተሠራው ኢትዮጵያዊ ፊልም የሆሊውድ አክተሮችን አስደነቀ

አፕራይት አፈይር ስሙ አልተለወጠም

እንዴዋን የሠሩት ፊልም ተጠናቋል

የሙዚቃው መፍትሄ ማጣት አማራቸዋል



# ኤሮቲካ

በጥላሁን ገሠሠ መወጋት ይነካካሉ የተባሉት ታምራት ላይኔ ማይሆኑ የቀድሞው መከላከያ ሚኒስትር ሥዬ አብርሃ መሆናቸው ተጠቆመ

ሚ.አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ አዲሱን የፓትሪያርክ ፓላስ ገነቡ

የከሰሰ ስጦታ እንደሚያበረክቱ ይጠበቃል

የድምፃዊውን 11 ሺህ ብር ክልክሎ የሚያስፈራራው ባለሙዚቃ ቤት ፍርድ ቤት ሊገተር ነው

በ«ሁናይት» ፊልም መዘረፍ

ከ40 ያላነሱ ግለሰቦች በስለር ተደርገዋል ተባለ

ድምፃዊት አበበች ደራራ አዲስ አበባ ገባች

በፈረንሣይ ኢትዮጵያውያን አርቲስት ከፍተኛ አድናቆት ተቸሩ

# ሜዲካል ጋዜጣ

ሜዲካል ጋዜጣ ሙሉ ትኩረቱን በሕክምና እና ስነልቦና ዘርፎች አድርጎ የሚሠራ የመጀመሪያው ጋዜጣ ሆኖ በማገልገል ላይ የሚገኝ ጋዜጣ ነው።



ሜዲካል

ሜዲካል መጽሔትን አርብ ይጠብቋት

በአሰበ ተፈሪ በመንታ ማህጸኗ መንታ የወለደችው ሴት የዶ/ር ቹን ውሳኔ ተቃወመች

የፍቅር፣ የተራክቦና የማህበራዊ ህይወቶች 10 ታላላቅ እንቆቅልሾችና ሳይንሳዊ ፍቻቸው

በ2003 የኤድስ መከላከል በኢትዮጵያ አበረታች ውጤትን ማሳየቱ ተጠቆመ

ሴት ለሚፈልግ ሴት፣ ወንድ ልጅም ለሚፈልግ ወንድ የሚያስወልድ ቴክኖሎጂ መጣ

መ...መ...መንተ...ባተብ ከድምፆች ጋር የሚፈጠር ግብግብ



ሜዲካል

በድንግልና እርግዝና ሊፈጠር ይችላል?

ያዳምጡ!!! 100 ዓመት መኖር ይፈልጋሉ?

ኬሚካሉ በአገራችን ምን ውስጥ እንደሚገኝ ያውቃሉ?

100 ዓመትና ከዚያም በላይ ለመኖር የሚያስችሉ 14 ሳይንሳዊ ጥበቦች ይፋ ሆኑ

10 ታላላቅ የማንነታችን ውስብስብ እንቆቅልሾች

ይመልከቱ!

# አዲስ አድማስ ጋዜጣ



ቅዳሜ ኅዳር 6/1992

አዲስ አድማስ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኞችን አሰናበተ

በመጪዎቹ ዓመታት የበርበሬ ዋጋ ይጨምራል



ቅዳሜ ሰኔ 17 1992

አዲስ አድማስ

«የሬሳ ክምር አየን ኢትዮጵያውያን ቅጣቱን አበዙት»

«የተሰነዘ ውጊያ የጨበጣ ነበር»

ወርልድ ስፔስ ያመጣቃቸው ሳተላይቶች አትራፊነታቸው አጠራጣሪ ነው ተባለ

«በሰላም አስከባሪ ሐይሉ እንዲሳተፉ የማንፈልጋቸው ሐገሮች አሉ »

One touch
One click
Union Dental Clinic



እንኳን ለብርሃን ልደቱ አደረሳችሁ! ቅዳሜ ታህሳስ 28 ቀን 1993
አዲስ አድማስ
«የኢትዮጵያ ንግድ ከፖለቲካዊ አድልዎ ጋር መታገል ግድ ሆኖበታል»
«ኢትዮጵያ አስተማማኝ የወደብ አገልግሎት ማግኘት አልቻለችም»
«ወሳኝ በሆነው የወረዳና የቀበሌ ምርጫ አባሎቻችን እየተዋከቡ ነው» ኢዴፓ
የስፖርት ኮሚሽኑና ፓርላማው አስቀየሙ
የሰላም አስከባሪ ኃይሉ እየተሟላ ነው
«ከተመረጥኩ ለአነስተኛና ለመካከለኛ ንግድ ትኩረት እሰጣለሁ»
«ታምራት የተባለ የሽልማት ድርጅት አቋቁመናል»
መልካም ዜና